# አሮጌው የአከሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር ቦርድ በተመለከተ

በመንግሥት ተቋቁሞ የነበረው ዓብይ ኮሚቴ አክሰስ ሪል እስቴት ያልከሰረ መሆኑን አረጋግጧል። አክሲዮን ማኅበሩም ከስሪያለሁ ብሎ በፍርድ ቤት ያስወሰነበት ሁኔታም የለም። ችግር ሆኖ የቆየው የባለአክሲዮኖች፣ የቤት ገዢዎችና የሌሎች ሶስተኛ ወገኖች መብቶችና ግዴታዎች ከግል ጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ አመራር ሰጭ አካል መጥፋቱ ነው። ከአስር ዓመት በላይ በቦታው የቆዬው አሮጌው የአክሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ቦታ ይሰጥና ራሳችን እንሠራለን ከሚሉ ቡደኖች ወግኖ ከመንቀሳቀስ በስተቀር የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ አያውቅም።

ይኽም እያለ አንዳንድ ቤት ገዢዎች ከቦርዱ ጋር አብሮ የመሥራት ዕድል ሊኖር ይችል እንደሆነ እንዲታይ በጠየቁት መሠረት የማኅበራችን አባሎች በግለሰብ ደረጃ ከሚያውቁዋቸው የቦርድ አባሎች ጋር በመገናኘት፣ እንዲሁም የማኅበራችን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደብዳቤ ጽፎ በመጠየቅ ተሞኩሯል። የተገኘው መልስ ግን ከኛ ጋር ለመሥራት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንደሌለ በመሆኑ ሳይቻል ቀርቷል።

## ለመንግሥት ያቀረብነው አቤቱታ

የአክሰስ ቦርድ ራሱ ለመፍትሄ መገኘት እንቅፋት መሆኑ ከታወቀ በኋላ የቀረን አማራጭ ቦርዱ በሌላ አዲስ ቦርድ እንዲተካ መጠየቅ ሆኖ አገኘነው። በመሆኑም የአክሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር ባለአክሲዮኖች ስብሰባ ተጠርቶ አዲስ ቦርድ እንዲቋቋም ለመጠየቅ ተገደናል። የጉዳዩ ባለቤት የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በመሆኑም አቤቱታችንን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አቅርበናል። የሚኒስቴሩ ባለሙያዎች የራሳቸውን ጥናትና የመረጃ ማሰባሰብ ካደረጉ በኋላ የተለያዩ ባለድርሻ የተባሉ ወገኖች አነጋግረዋል። ባለአክሲዮኖችም የራሳቸውን እንቅስቃሴ በማድረግ ከ10% በላይ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ ተደርጎ አዲስ ቦርድ ሊመረጥ ችሏል።

በመሆኑም ቤት ገዢዎች ለአዲሱ የዳይረክተሮች ቦርድ ተባባሪ በመሆን ሰጥቶ በመቀበል መርህ በመደራደር ቤታችን ተሠርቶ እንዲሰጠን በትዕግሥት መጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ማኅበራችን ያምናል።

ሰኔ 2015 ዓ.ም.

# የማኅበራችን እንዲሁም የኢንተርኔት የውይይት ቡድናችን አባል ይሁኑ

የውይይት ቡድናችን አባል መሆን ጥቅሙ፦

1. በሚደረጉት ውይይቶች ለመሳተፍ እንዲችሉ። የሚሰጡት ሐሳብ ባይኖርዎት እንኳ ሌሎች ቤት ገዢዎች የሚሉትን ለመከታተል ያስችልዎታል።
2. ብዙ ቤት ገዢዎች ውጭ አገራት ስለሚኖሩ በቀላሉ ለመገናኘት ያስችላል።
3. ወቅታዊ መረጃዎች ለመለዋወጥ ያስችላል።
4. በተለይ ከማኅበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጋር የሚደረገው ግንኙነት የወረቀት ሥራን በማስቀረት ወጪ ለመቆጠብ ያስችላል።

ስለዚህ እርስዎም የበኩልዎን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንዲችሉ በቅድሚያ ወደ ኢንተርኔት የውይይት ቡድናች ይቀላቀሉ። በመቀጠል የማኅበራችን አባል እንዲሆኑ ግብዣ ይላክልዎታል። ወደ ኢንተርኔት የውይይት ቡድኑ ለመግባት ቀጥሎ ካሉት ሁለት መንገዶች አንዱን ይጠቀሙ።

1. ወደ ኢንተርኔት ቡድናችን የመረጃ መረብ በመሄድ ያመልክቱ። አድራሻው፦ https://accesshomebuyers.groups.io/g/main የሚል ነው። ገጹ ላይ ወደታች ትንሽ ወረድ ብሎ + Apply For Membership in this Group የሚለውን ቁልፍ ጠቅ ካደረጉ በኋላ ቀጥሎ በሚመጣው ገጽ ላይ ያለውን በመሙላት መልዕክት ይላኩ።
2. access_home_buyers@yahoo.com ወደሚለው የኢሜይል አድራሻችን መልዕክት በመላክ መጠየቅ ይችላሉ።

ቤት ገዢ መሆንዎን አውቀን በፍጥነት እንድናስተናግድዎት፦

- ከአክሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር ጋር የተፈራረሙት ውል ሁሉም ገጾች በጥሩ ሁኔታ የተሠራ ስካን ፎቶ ኮፒ፤
- ለገዙት ንብረት ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የከፈሉበት ደረሰኝ ስካን ፎቶ ከፒ፤

ይላኩልን።

ለበለጠ መረጃ
https://www.arehba.org
የሚለውን የመረጃ መረባችን ይጎብኙ።




## መግቢያ

አክሰስ ሪል ስቴት አክሲዮን ማህበር ከቤት ገዥዎች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት የገባውን ቃል ሳይፈጽም ሲቀርና የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ከአገር ከወጡ በኋላ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ያካተተ "አብይ ኮሚቴ" ተቋቁሞ ነበር። ይህ ኮሚቴ ችግሩን በማጥናት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን የማቅረብ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ይሁን እንጂ ኮሚቴው ከቤት ገዢዎች ጋር አንድ ጊዜ ስብሰባ አድርጎ ኩባንያው እንዳልከሰረ ካረጋገጠ በኋላ ሌላ ስብሰባ ለማድረግ ለቤት ገዥዎች የገባውን ቃል ሳያከብር እራሱን እንዳፈረሰ አንዳንድ የቤት ገዢዎች ተረዱ።

ከዚያም ከቤት ገዢዎች ተወካዮች ኮሚቴ መካከል አንዳንዶቹ ራሳቸውን "አብይ ኮሚቴ" ብለው ከፈረጁ በኋላ በመንግስት የተቋቋመው ከፍተኛ ኮሚቴ ሥራውን ጨርሶ መፍረሱን ላልጠረጠሩ ቤት ገዥዎች ኮሚቴው ያለ በማስመሰል ውዥንብር መፍጠር ጀመሩ። በቀጣይም ቤት ገዥዎች በራሳቸው ቤት ለመገንባት ተስማምተዋል እና መሬቱ እንዲሰጣቸው በማለት መንቀሳቀስ ጀመሩ። እውነታው ግን የቤት ገዢዎችን ሰብስቦ መሬቱ ይሰጠንና ቤታችንን ራሳችን እንሠራለን ማለት አለማለታቸውን የጠየቃቸው ወገን አልነበረም።

የቤት ገዢዎች ተወካዮች ኮሚቴ ፍትሃዊ የሆነውን የቤት ገዢዎች ጥያቄ፣ ማለትም "አለምንም ተጨማሪ ክፍያ በውላችን መሠረት ቤቱ ተሠርቶ እንድንረከብ" የሚለውን ወደጎን በማድረግ የተወሰኑ

የቤት ገዢ ወኪሎችን እና የቦርድ አባላትን በማስተባበር ጠያቂና ተጠያቂ በመደባለቅ ኩባንያው በሕግ አግባብ ባልፈረሰበት ሁኔታ መሬቱ ተላልፎ ይሰጠን እና በራሳችን እንሠራለን በማለት ለ10 ዓመት ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል። ይህ አቋማቸው የንግድ ሕግን የሚያፋልስ፣ ከባለአክሲዮኑ ጋርም ቅራኔን የሚፈጥር በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ የማይገባው ነው። ይህንን ተከትሎም እራሱን "እውነተኞች ቤት ገዢዎች" እያለ የሚጠራው የቤት ገዢዎች ቡድን ብቅ አለ። ይህ ቡድን ራሱን "አብይ ኮሚቴ" እያለ የሚጠራውን ቡድን እንቅስቃሴ በመቃወም እንዲሁም የመልዕክት መላኪያ ዝርዝሮችን ፈጥሮም የቤት ገዢዎችን ማነጋገር ጀመረ።

ስለዚህ፣ የኢንተርኔት ቡድን በመፍጠርና ሁሉም የታወቁ የኢሜል አድራሻዎች ያላቸው የቤት ገዢዎች የኢንተርኔት ቡድኑን እንዲቀላቀሉ ግብዣ ተላከ። በዚህ መንገድ ይህ አዲስ ቡድን "አብይ ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራው ኮሚቴ በቤት ገዢዎች ላይ የጫነውን የመረጃ ሞኖፖሊ አፍርሷል። አሁን፣ የቤት ገዢዎች፣ የትም ሀገር ቢኖሩ፣ ከሌሎች የቤት ገዢዎች ጋር ሃሳብ መለዋወጥ ይችላሉ።

የቤት ገዢዎች ኢንተርኔት ቡድኑ የቤት ገዢዎች ብዙ ጥሩ ሃሳቦችን እንዲለዋወጡ ያስቻለ ቢሆንም ችግሩ ጥሩ፡ ጥሩ ሃሳቦችን ተከታትሎ መሬት ላይ ወርደው ወደ ተግባር እንዲገቡ የሚያደርግ አካል ያለመኖሩ ነበር። ስለዚህ አንዳንድ የቤት ገዢዎች "ማህበር" እንዲቋቋም ባቀረቡት ሃሳብ መሠረት የአክሰስ ሪል እስቴት ቤት ገዢዎች ማኅበር ተቋቁሞ ጥቅምት 2 ቀን 2013 ዓ.ም. ምስክር ወረቀቱን ተቀብሏል።

## አቤቱታ (Petition)

የቤት ገዢዎች ኮሚቴው ከአንዳንድ የአክሰስ ኩባንያ ቦርድ አባሎች በማበር እውነተኞቹ ቤት ገዢዎች ያልጠየቁት እንደጠየቁ ተደርጎ ቦታ ይሰጠንና ቤታችንን ራሳችን እንሠራለን ያሉ በማስመሰል በጋዜጣ ጭምር መግለጫ እስከ መስጠት ደርሰው ነበር። ይህንን አካሄድ የሁሉም ቤት ገዢዎች ፍላጎት ባለመሆኑ በ"እውነተኞች ቤት ገዢዎች" ቡድን የተጀመረው ቤት ገዢዎች የሚፈልጉት ቦታ ሳይሆን ከአክሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር ጋር የገቡት ውል ተከብሮ ንብረታቸውን ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ ማግኘት መሆኑን የሚገልጽ የአቤቱታ ፊርማ የማሰባሰብ ተግባር በኢንተርኔት የውይይት ቡድናችን በኩልም በማስተባበር 523 ቤት ገዢዎች የፈረሙበት አቤቱታ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ገቢ አድርጓል። በመቀጠልም ለአቤቱታችን ተፈጻሚነት ውጭ አገራት ያሉት አባሎቻችን በየኤምባሲዎች በኩልና በዳያስፖራ ጽሕፈት ቤት በኩል፣ አገር ውስጥ ያሉት አባሎቻችን ደግሞ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በማዳረስ ሲከታተሉ ቆይተዋል።

## የማኅበር መቋቋም

ከላይ በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው በኢንተርኔት የውይይት ቡድናችን በኩል ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦች እየተነሱ የነበሩ ቢሆኑም ለተግባራዊነታቸው መሬት ላይ በቋሚነት የሚከታተል አካል ያልነበረን በመሆኑ መና እየሆኑ ይቀሩ ነበር። በመሆኑም ማኅበር ይቋቋም የሚለው ሃሳብ አስፈላጊነት እየጎላ በመምጣቱ 43 የቤት ገዢዎች የማህበሩ መሥራቾች ሆነው ለመሥራት ፈቃደኛ ሆነዋል። ከነዚህ መካከል በአዲስ አበባም ሆነ በውጪ የሚኖሩ የቤት ገዢዎች ይገኙበታል። እነዚህ ቤት ገዢዎች በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ፎርም እንዲሞሉ እንዲሁም መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ወዘተ. የመሳሰሉትን የመታወቂያ ሰነዶችን እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸው ነበር። ነገር ግን፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ 26 የቤት ገዢዎች ብቻ ሁሉንም መስፈርቶች በማሟላት ፊርማቸውን በመሥራችነት ማስቀመጥ የአክሰስ ሪል እስቴት ቤት ገዢዎች ማኅበር አቋቁመዋል።

በቀጣይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ የተካሄደ ሲሆን የማኅበሩ የሥራ ሃላፊዎችም ስለራሳቸው ለሲቪል ማህበራት ድርጅት ባለሥልጣን ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል።

## ጽሕፈት ቤት ማደራጀት

ከዚያም የቢሮ ቦታ ተከራየን፤ በተጨማሪም አንዳንድ አባሎቻችን በበጎ ፈቃደኝነት ገንዘብ በመሰብሰብ ለቢሮአችን አገልግሎት የሚውሉ ሁለት ላፕቶፖችን ገዝተዋል።

በመጀመርያ በሥራ ዲሬክተርነት የሚያገለግል ተገቢው ብቃት ያለው አንድ ሰው ተገኝቶ የነበረ ቢሆንም የጠየቀው ክፍያ ከገንዘብ አቅማችን በላይ ስለነበር የነበረንን የገንዘብ አቅም ባገናዘበ ለመሥራት የተስማማ አንድ አመልካች ተቀጥሮ ለአራት ወራት ሠርቷል።

በአሁኑ ጊዜ ግን ሙሉ ጊዜውን የሚሰራ ዳይሬክተር የተቀጠረ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የቢሮ ረዳት የቀጠርነው የካቲት 2013 ውስጥ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቢሮ ረዳት ቅጥር ቀጥሏል።

## ግንኙነቶች ማካሄድ

የቤት ገዢዎችን ለማግኘትና ወደ ቡድናችንና ማህበራችን እንዲቀላቀሉ ለማሳሰብ የተለያዩ መንገዶችን ሞክረናል። ቡድኑ የካቲት 2010 ዓ.ም. እንደተቋቋመ ከ1,500 በላይ ለሆኑ ቤት ገዢዎች ኢሜይል በመላክ የቡድናችን አባሎች እንዲሆኑ ጋብዘናል።

በኢሳት ቲቪ (በእያንዳንዱ ለአምስት ጊዜ የተደገመ የሁለት ዙር ማስታወቂያ)፣ በሸገር ኤፍ ኤም ራዲዮ በማስነገር የቤት ገዥዎች ወደ ቡድናችንና ማህበራችን እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቅርበናል። እንዲሁም አባሎቻችን ለሌሎች ላልሰሙ ቤት ገዢዎች እንዲነግሩ በማድረግ መረጃ እንዲደርሳቸው አድርገናል።

በጉዳዩ ያገባናል የሚሉ ወገኖችን ሁሉ በማነጋገር አብረውን እንዲሠሩ ስንጠይቅ ቆይተናል።

እንዲሁም ከቤታችን ጋር በተያያዘ ያሉብንን ችግሮች ለመፍታት ይረዳሉ ብለን የምናምንባቸውን ሁሉንም የመንግስት መሥሪያ ቤቶች አነጋግረናል፤ አሁንም እያነጋገርን እንገኛለን።

## ራሱን "ዓብይ ኮሚቴ" እያለ የሚጠራውን ቡድን በተመለከተ

ከመንግሥት በተሰጠ መመሪያ መሠረት በተቋቋመው ዓብይ ኮሚቴ ውስጥ ከቤት ገዢዎች ተወካዮች ኮሚቴም አንድ ሰው እንዲካተት ተደርጎ ነበር። ዓብይ ኮሚቴው ተግባሩን ማጠናቀቁን ካስታወቀበት ከግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ.ም. በኋላ በቤት ገዢዎች ስም በዓብይ ኮሚቴው ውስጥ ተወክሎ የነበረው ግለሰብ ከአንዳንድ የአክሰስ ሪል እስቴት አክሲዮን ማኅበር የቀድሞው ቦርድ አባሎች ጋር ግንባር በመፍጠር ሥራውን አጠናቆ የተበተነውን ዓብይ ኮሚቴ ስም በመጠቀም ውዥንብር ሲፈጥር ቆይቷል።

አንዳንድ ቤት ገዢዎች ከዚህ ቡድን ጋር ተቀራርቦ መሥራቱ ሊጠቅም እንደሚችል የሚያምኑ አልጠፉም። በኛ በኩል እነዚህ ቤት ገዢዎች ላቀረቡት ሃሳብ አክብሮት በመስጠት ከቡድኑ ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት እንዲቻል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። በተለያዩ ውጭ አገራት የሚኖሩ አባሎቻችን ወደ አገር ቤት በመጡባቸው ወቅቶች እነሱን በማስተባበር ከቡድኑ መሪዎች ተገናኝተው ተቀራርቦ ለመሥራት በሚቻሉባቸው ሁኔታዎች እንዲነጋገሩ ተደርጓል።

የማኅበራችን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴም የቡድኑ መሪን በስልክ፣ ደብዳቤ በመጻፍ እና በአካል በመገናኘት አብሮ ለመሥራት ስለሚቻልበት ሁኔታ በመነጋገር ጥረት አድርጓል።

ነገር ግን ቡድኑ ከኛ ጋር ለመሥራት በፍጹም ፍላጎት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል። ይባስ ብሎም የአገራችን ፓርላማ ባጸደቀው ሕግ መሠረት የተቋቋመውን ማኅበራችንን እና መሪዎቹን እንደ አጭበርባሪዎች በመቁጠር በአክሎግ ስዩም ተፈርሞ በማኅበራዊ ሚዲያ ተሰራጭቶ ታይቷል።